ኅዳር፴፥ ፳፻፯ዓ. ም.

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ።**
**በስማ ለእግዝእትነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ እምነ ወንግሥትነ**
**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ፥ ካህንነ፥ ወንጉሥነ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ።**

ይድረስ፡ እጅግ ለተከበርክና ለተወደድክ እንዲሁም ለምትናፈቀዉ ቅንና እዉነተኛ፥ ትሁትና ታማኝ፥ ርኅሩና ትጉኅ የመንግሥተ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ አገልጋይ ኪዳናዊ ወንድሜ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ! ከተከበሩትና ከሚወደዱት ኪዳናዉያትና ኪዳናዉያን ቤተሰቦችህ ጭምር እንደምን ሰንብታችኋል? እኔ ቸሩ መድኃኔዓለም ከነእናቱ ድንግል ማርያም ይመስገን ከኪዳናዉያን ቤተሰቦቼ ጭምር እጅጉን ደህና ነኝ፡፡

በኅዳር ፳፮፥ ፳፻፯ ዓ.ም የተጻፈዉ ደብዳቤህ በአ-ጦማር አድራሻዬ ደርሶኝ አነበብኩት፡፡ ስለሁም እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ፡፡ አሁንም እናትና ልጅ እንደ ቀድሞዉ በዉስጤ ለተፈጠረዉ ጥያቄና ፈተና በአንተላይ አድረዉ ምላሽ ሰተዉኛልና አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ታዲያ ዉስጤ ሲታወክና ሲቸገር እንዲሁም በጥያቄ ስወጠር እግዚአብሔርና እመቤታችን ምላሽ በሚሰጡኝ በኩል ጥያቄዬንና ስሜቴን ማቅረቤ አግባብነት እንዳለሁ በአንተም ዘንድ ስለተረጋገጠልኝ እጅጉን ደስ ብሎኛል፡፡ ደብዳቤ ልዉዉጣችንን እንኳ ስገመግመዉ እኔ ጥያቄዬን ያቀረብኩትና አስተያየቴን የሰጠሁት እንደልጅነቴና ጎረምሳነቴ ቆጣ ባለ ስሜት ሲሆን አንተ ደግሞ የሰጠኸኝ ምላሽ እንደ አምላክህና አባትህ እግዚአብሔር እንዲሁም እንደ እናትህና እመቤትህ ቅድስት ድንግል ማርያም በፍቅርና በርኅራኄ እንዲሁም በጸጋና በሙሉ እዉነታ ነዉ፡፡ መቼስ "ፈቃደሥላሴ እንደ እኔ መሆን አለበት፥ እንደኔ ብቃት ማሰየት አለበት" እንደማትል አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም እንደ ወጣኒነቴ (ጀማሪነቴ) ከእኔ የሚጠበቅ የድክመት አስተሳሰብ፥ አቋም፥ ጽናት፥ ትጋት አለና፡፡ ነገር ግን እስከ አሁን እንደምታደርገዉ አርአያ በመሆን፥ በማስተማር፥ በማብራራት እንዲሁም በጸሎት በመደገፍ አንድ ወጣኒን ለብቃት እንደምታበቀዉ እተማመናለሁ፡፡

ዉስጤ የከነከነችኝና ጥያቄ የፈጠረችብኝ ምላሽህ እንደ ቀደሙት ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና እንደ አይሁድ ካህናት እንዲሁም እንደዘመኑ አስመሳይ አገልጋዮችና እዉቀታቸዉን እንደሚያመልኩት ሰዎች ቃላት በመሰንጠቅ የሥጋና ደም ስሜቴን ልገልጽበትና አንተን ልኮንንበት እንዳልሆ እዉነተኛ ምላሽህ ምስክር ነዉ፡፡ ምክንያቱም የተሰጠኝ ምላሽ የሥጋና የደም ስሜት ያልሆነ የእዉነት ባለቤት የሆነዉ የመንፈስ ቅዱስ ነዉና፡፡ ያን ያህል ሲከነክነኝና ጥያቄ ሲፈጥርብኝ የቻለዉ ደግሞ በአንተ በኩል በጽሑፍ ሆነ በቃል፥ በምስል፥ በመጻሕፍት የቀረቡ መልእክቶች ሆነ ትምህርቶች "ንቡረ እድ ኤርሚያስ የተናገረዉ ነዉ፥ ያዘዘዉ ነዉ... ወዘተ" በማለት ሳይሆን የማነበዉና የምሰማዉ እንዲሁም የምመለከተዉ፡ " እርሱ እግዚአብሔር ነዉ የተናገረዉ ወይንም እመ አምላክ ናት የተናገረችዉ " በሚል እምነት ስለሆነ ነዉ፡፡

የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር እንዲሁም ርኅራኄና ይቅርባይነት ባይኖር ኖሮ ስለ እዉነት እኔ አሁን ሳለሁበት ሕይወት ባልበቃሁ ነበር፡፡ ካለ አድሜያቸዉ በሥጋ ሞት እንደተለዩኝ ወንድሞችና እህቶች ለንስሐ ሳልበቃ ከነኃጢአቴ በተጠራሁ ነበር፡፡ ምክንያቱም እዉነትን እያወኩ፥ በንስሐ ተመልሼና ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን ከተቀበልኩ በኋላ በሥጋ ድካም ወደ ትፋቴ ተመልሼ ነበርና፡፡ አሁንም ዋስትናዬ እመ አምላክ እመቤታችን ድንግል ማርያምና ቅዱሳን ናቸዉ እንጂ ነገ ምን እንደምሆን ምን እንደማደርግ አላዉቅም፡፡ አሁንም ከተግባር ሆነ ከንግግር እንዲሁም ከሓሳብ ኃጢአት ነጻ ነኝ አልልም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለምፈጽመዉ በደል ይቅር እንዲለኝና እንደ እርሱ ፈቃድ ብቻ እንድመላለስና በቀሪ ዘመኔም የእርሱን ፈቃድ ብቻ ፈጻሚ፥ አስፈጻሚ እንድሆን ነዉ ዘወትር የምለምነዉ፡፡ የዛሬ አሰራ አራት ዓመት ገዳማ እግዚአብሔር፤ ሰዉ በራሱ ሥልጣንና ትጋት እንዲሁም ጥንቃቄ ብቻ ከኃጢአት መጠበቅ እንማይችል ፤ በመዉደቅና በመነሳት ሕይወት ዉስጥ አስተምሮኛል፡፡

እዚህ ላይ የሰዉ ዘሮች ሁሉ ንስሐ እንደሚያስፈልጋቸዉ የሚገልጸዉን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል አቀርባለሁ፡ "በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተዉ ጲላጦስ ደማቸዉን ከመሥዋዕታቸዉ ጋር ስለደባለቀዉ ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት፡፡ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸዉ ፡- እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለደረሰባቸዉ ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን? እላችኋለሁ፥ አይደለም ነገር ግን <u>ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ  እንዲሁ ትጠፋላችሁ</u>፡፡  ወይስ በሰሊሆም ግንቡ የወደቀባቸዉና የገደላቸዉ እነዚያ አሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ፡፡" ሉቃስ<u>፲፫፥፩-፭</u>

ሴላዉ ጋሽዬ ጥያቄዬንና ቅሬታዬን ያቀረብኩት ያን እጅግ ጥብቅ የሆነዉን ትምህርት ዘንግቼ አይደለም፡፡ ያ ብቻ አይደለም እግዚአብሔርና እመቤታችን በአንተ ላይ አድረዉ ለትዉልዱ መልእክታቸዉን እንደሚያስተላልፉ ዘንግቼ አይደለም፡፡ ጌታችን ለሐዋርያነትና ለደቀመዛሙርትነት የመረጣቸዉ እነዚያን በጽድቃቸዉና በእዉቀታቸዉ የሚመጻደቁትን ጸሐፍት ፈሪሳዉያንን ሳይሆን፤ ከእዉቀት እዉቀት የላቸዉም የተባሉትን እንዲሁም ኃጢአተኛ፥ ቀራጭ፥ ዘማዊ የተባሉትን በፍቅርና በርኅራኄዉ አቅርቦ ያለፈዉን በደላቸዉን ይቅር ብሎ ቅንና የዋህ አስተሳሰባቸዉን መርጦ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡ አሁን ደግሞ እጅግ የትየለሌ የሆነዉን ርኅራኄዉንና ፍቅሩን በአንተ ተተንትኖ በቀረበዉ ምላሽህ የበለጠ ተረድቻለሁ፡፡  ጥያቄ ያስነሳብኝ ምላሽህም ምስኪን የሆነዉንና እዉነተኛ እረኛ አቶ ለተቅበዘበዘዉ  እንዲሁም ሸክም ለከበደዉና ሸክሙን የሚያቀልለትን ለሚፈልገዉ ትዉልድ፤ በፍቅርና በርኅራኄ ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብና ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ለማብቃት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡ በተለያየ መንገድና አቅጣጫ በእዉነተኛዉ አገልግሎትህ ዉስጥ የሚደርስብህ ፈተናና ጥቃት እንዲሁም

ስሜት መጎዳት ሳያንስህ እኔ ደግሞ ስሜትህን ጎዳሁ ብዬ በዉስጤ አዝኛለሁ እንባዬም እንደፈሰሰ ሳልገልጽልህ አላልፍም፡፡ እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ የቀረበኝና ስራዉን ያሰራኝ በርኅራኄዉና በኃዘንተኛነት ስሜት ነዉ እንጂ በኃያልነቱና በታላቅነቱ ስላልሆነ ባለፉት ዓመታት በኃዘንተኛነትና በመከረኛነት ስሜት ያሳለፍኩት ለዚያ ነዉ፡፡

**ጋሽዬ፡** እንግዲህ ስሜትህን ጎድቼ ከሆነ እመ አምላክ እፁፍ በእፁፍ ታጽናናህ ትካስህ እላለሁ፡፡ በቀሪ ምድራዊ ዘመንህ የተጋደልክለት እዉነት ፍሬ አፍርቶ ታሳይህ፥ ትዉልዱን ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትና ተዋሕዶ ሃይማኖት ታብቃልህ፡፡ ሌላዉ የማቀርበዉ ሓሳብ ደግሞ የትየለሌ የሆነዉ የእግዚአብሔር ፍቅርና ርኅራኄ እንዲሁም ምሕረትና ቸርነት መጠቀሱ አግባብነት ያለዉ ብቻ ሳይሆን ግድ መገለጽ ያለበት መሆኑን አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም እርሱ እግዚአብሔር ሁሉን በአምላካዊ ሥልጣን ማድረግ ሲችል እኛን  ልጆቹን የቀረበን ራሱን ዝቅ አድርጎ በዝቅተኛ ቦታ ከመወለድ አንስቶ የተለያዩ ፈተናዎችንና መከራዎችን በመቀበል እስከመስቀል ድረስ ነዉና፤ ይህ አፍቃሪና ርኅሩኅ አምላክ ፍቅሩና ርኅራኄዉ እንዲህ ተብሎ ሲገለጽ የማይችል ከአእምሮዋችን በላይ ነዉና፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ፍቅሩና ርኅራኄዉ የትየለሌ ቢሆንም ፍርዱም እጅግ ጥብቅ መሆኑ ለትዉልዱ መገለጽ ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጭምር ሕያዋን ፍጥረቶቹ ቢሆኑም በአንድ ጊዜ ጥፋታቸዉ ነዉ ወደዚህች ጎስቋላ ምድር የተጣሉትና ለገሰቆለ ባሕርይ የተዳረጉት፡፡ ያ ብቻም አይደለም በዓመፃ ላይ ዓመፃ ስለፈጸሙ የገሃነመ እሳት ፍርድ የሚጠብቃቸዉ፡፡ እንዲሁም አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት የመጀመሪዎቹ ሕያዋን የገነት ፍጡሮች አትብሉ የተባሉትን ፍሬ በመብላታቸዉ ነዉ ለጎሰቆለና ሳደፈ ባሕርይ የተዳረጉትና ለሲኦል ፍርድ የደረሱት፡፡ ያ ብቻም አይደለም ከዓመፃቸዉና ከክህደታቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ካልተመለሱ ለሰይጣናት የተዘጋጀዉ ገሃነመ እሳት ፍርድ እንደሚጠብቃቸዉ የተገለጸዉ፡፡ እንኳን በድፍረት በተግባር የሚፈጸም ኃጢአት ይቅርና " ወንድሙን ደንቆሮ" ብሎ የሚሳደብ የገሃነመ እሳት ፍርድ እንደሚጠብቀዉ ነዉ እግዚአብሔር በግልጽ በዘመነ ሥጋዌዉ ያስተማረን፡፡ " ለቀደሙት :- አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ÷ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለዉ ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ **ደንቆሮ የሚለዉም ሁሉ የገሃነመ እሳት** ፍርድ ይገባዋል፡፡ " ይላል፡፡ማቴ፭÷፳፩-፳፪

ከላይ ያለዉን ሓሳብ ያቀረብኩት አንተ ምድራዊዉን ሆነ ሰማያዊዉን  የእግዚአብሔርን እዉነተኛ ፍርድ አላቀረብክም  ለማለት ፈልጌ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር እንዲሁም ምሕረትና ርኅራኄ የትየለሌ እንደሆነ ሁሉ ፍርዱም እጅግ ጥብቅ መሆኑን ለራሴም ሆነ ለኪዳናዉያንና ለኪዳናዉያት ወንድሞቼና እህቶቼ ለማስታወስ ስለፈለኩ ነዉ፡፡ በአንተ በኩልማ ቅዱስ ኪዳኑን አንጠብቅም በማለታችን

ምክንያትና በእግዚአብሔር ላይ እየፈጸምን ባለዉ ዓመፃ፥ ክህደት፥  የአምልኮና የጋብቻ ምንዝራና ምክንያት መራራ ፍሬ እየጠጣን መሆኑን ትገልጽልን የለም ወይ! እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐ ተመልሰን ቅዱስ ኪዳኑን እንድንጠብቅ በጽሑፍም፥ በቃልም ሁሌ የምታሳስበን ጉዳይ መሆኑ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ለእኔ ምላሽ ግን የቸርነቱና የምሕረቱ እንዲሁም የፍቅሩና የርኅራኄዉን ባሕርይ ብቻ እንዲጎላ አድርገህ ማቅረብህ ትክክልና አግባብነት ያለዉ በመሆኑ እቀበለዋለሁ፡፡ ምክንያቱም በእኔ ጥያቄና አስተያየት ዉስጥ እጅግ ጥብቅ የሆነዉ ፍርዱ ነዉ የጎላዉ እንጂ ፍቅሩና ምሕረቱ እንዲሁም ርኅራኄዉና ቸርነቱ በሚገባ አልተገለጸምና፡፡

እኛ የአሁን ትዉልዶች አንቱ በተባሉ መምህራንና ሊቃዉንት ሳይቀር የተሳሳተ እዉቀትና አመለካከት እንድንይዝ መደረጉ ከአንተ በላይ የሚያዉቅ ሰዉ የለም፡፡ ለምሳሌ ባለፈዉ ዓመት አንድ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር የአብነት ትምህርት ጭምር በሚገባ የተማሩ "በጾም ወቅት ግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ ይፈቀዳል አይፈቀድም?" ተብለዉ በአንድ በቅድስት በቤተክርስቲያን ስር ባለ ማኅበር በሚታተም ጦማር ላይ ለተጠየቁት ጥያቄ መላሽ የሰጡት " በጾም ሆነ በበዓላት ጊዜ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ኃጢአት ነዉ "ያሉት፡፡ ታዲያ እሳቸዉም ከራሳቸዉ ያመጡት አይመስለኝም ከመምህራኖቻቸዉ ያገኙት ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን በራሴ ስገምተዉ ለአፋቸዉ ተናገሩት እንጂ ራሳቸዉም እንደማይፈጽሙት እገምታለሁ፡፡ ምክንያቱም የጾምና የበዓላትን ቀናት ብንደምራቸዉ በዓመት ዉስጥ ነጻ የሚሆኑት ቀናት አንድ ወር ቢሆን ነዉና፡፡ ታዲያ ይህን የተሳሳተ እዉቀትና አመለካከት የሚቃወም ቢኖር ደግሞ " መናፍቅ፥ ከሃዲ፥ ወይንም አህዛብ ነዉ" የሚባለዉ፡፡እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን፥ አይሁድ ካህናት ራሳቸዉ የማይሸከሙትን ሸክም በምዕመን ላይ የሚጭኑ ትብታብ የሚተበትቡ ብዙ "እረኞችና አዋቂዎች ነን" የሚሉ ናቸዉ በተለያየ የኃላፊነትና የአገልግሎት ወንበር ላይ የተቀመጡት፡፡

አምላካችን ሰዉ ሆኖ በግልጽ ያስተማረዉን " ሕዝቡንም ጠርቶ ፡- ስሙ አስተዉሉም፤ ሰዉን የሚያረክሰዉ ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣዉ ግን ሰዉን የሚያረክሰዉ ይህ ነዉ አላቸዉ፡፡ በዚያን ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ቀርበዉ ፡- ፈሪሳዉያን ይህን ቃል ሰምተዉ እንደተሰናከሉ አወቅህን? አሉት፡፡ እርሱ ግን መልሶ ፡- የሰማዩ አባቴ ያልተከለዉ ተክል ሁሉ ይነቀላል፡፡ ተዉአቸዉ ዕዉሮችን የሚመሩ ዕዉሮች ናቸዉ፤ ዕዉርም ዕዉርን ቢመራዉ ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ አለ፡፡ጴጥሮስም መልሶ ፡- ምሳሌዉን ተርጉምልን አለዉ፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- እናንተ ደግሞ እስካሁን የማታስተዉሉ ናችሁን? ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ አልፎ ወደ እዳሪ እንዲጣል አትመለከቱምን? ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰዉንም የሚያረክሰዉ ያ ነዉ፡፡ ከልብ ክፉ ሓሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በዉሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና፡፡ ሰዉን የሚያረክሰዉ ይህ ነዉ እንጂ ባልታጠበ እጅ መብላትስ ሰዉን አያረክሰዉም" ማቴ፲፭፥፲-፳ የሚለዉን የእዉነት ቃል ለምን

እንደማያስተምሩ አልገባኝም፡፡ ዋናዉ ርኩስ የሚያስበልንና እንደ ሰይጣናት የሚስቆጥረንን የዓመፃና የክፋት ተግባርንና ሓሳብን ከቁም ነገር ሳይቆጥሩ እንደ ኃጢአት ሆነ እንደ ርኩሰት የማያስቆጥረዉን እግዚአብሔር የፈቀደዉን ሥርዓት ስምን እንደሚኮንኑ ግራ ያጋባል፡፡ ምዕመናን ይህን አለማወቅን ቢናገሩ ብዙም ሳያስገርም ይችላል፡፡ ምክንያቱም እንደ ትዉፊትና ልማድ ከወላጅ ወደ ልጅ ሲተላለፍ የቆየ አጉል ልማድነዉና፡፡ ነገር ግን ወንጌልን በሚገባ ማወቅ ብቻ አይደለም ተንትነዉ የሚያስተምሩ ምሁርና ሊቅ የተባሉት አገልጋዮች ይህን የተሳሳተ ትምህርትና አስተሳሰብ እዉነተኛ ትምህርትና አስተሳሰብ አድርገዉ በሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን ላለ ትዉልድ ሲያስተላልፉ እጅጉን ይገርማል፤ ያሳዝናልም፡፡

" ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለዉ ምን እንደሆነ ብታዉቁስ ኃጢአት የሌለባቸዉን ባልኮነናችሁ ነበር" ማቴ ፲፪፥ ፯-፰ ያለዉን የጌታን ቃል ቢያስተዉሉ መልካም ነበር፡፡

ጋሸዬ፡ ከአንተ የምንጠብቀዉ እንዲህ በተሳሳተ እዉቀትና አስተሳሰብ የተበከለዉን ሕሊናችንና የተሳሳተ እዉቀትና አስተሳሰባችንን በትምህርትና በመልእክቶችህ እንድታስተካክለዉና ወደ ሙሉ እዉነት እንድታደርሰን ነዉ፡፡ ታዲያ ተማሪ ግልጽ ያልሆነለትን አስተምሪዉን ልክ እንደ ደቀመዛሙርቱ መጠየቁ አይቀርምና ሳትሰለችና ሳትታዘበን ጊዜ ስታገኝ ማብራሪያህን እንደምትሰጠን እንተማመናለን፡፡

ከዚያ ጋር አያይዤ የምጠይቅህ ጥያቄ በዚሁ ባለማወቅና ባለማስተዋል እንዲሁም ባለመረዳት ስሜት ነዉና ጊዜ ስታገኝ በግልም ይሁን እንዲሁ በማኅበር ማብራሪያ እንደምትሰጠን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ይኸዉም

**"በስሕተትና ባለማወቅ፥ ያለፈቃድ ተገድዶና ተታልሎ፥ ወይም፡ሳያውቁ፡ በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት፡ የሚፈጸመው ጥፋት፡ በደል፥ ወይም፡ኃጢኣት አይደለም። ይህ እውነታ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ ሰዎች እንኳ፡"ፍትሕ ርትዕ" ብለው በሚያካኺዱት ሥርዓታቸው፡ ሲሠሩበት ይታያል።" የሚለዉ ነዉ፡፡**

ምድራዊዉ ሥርዓትና ፍርድ እንደሰማያዊ ሥርዓትና ፍርድ መሆን ቢጠበቅበትም እዉነት ስላልነገሡችና ቦታዉን ሐሰት ስለያዘች አድሎና መድሎ ያለበት እንዲሁም የተሳሳተ ፍርድ ሲሰጥ በየጊዜዉ የሚታይ ቢሆንም፤ በዓለማዊ ሆነ መንፈሳዊ በተባለዉ የሕግ ሥርዓት በስህተትና ባለማወቅ ያለፈቃድና ተገድዶ፥ ተታልሎ እንዲሁም በድንገተኛና በገነፈለ ስሜት የሚፈጸም ጥፋት ሆነ በደል ፍርዱን ሲያቀለዉና ቀላል ከሆነም ሊያስምረዉ እንደሚችል ቢታወቅም በፈጸመዉ ድርጊት ግን ማንም ቢሆን ከተጠያቂነት እንደማይድንና እንደ ጥፋቱ ደረጃ እንደሚጠየቅ ይታወቃል፡፡ እንዲሁም አንድ ሰዉ እንደ ክርስቲያንነቱ ወይንም እንደ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አባልነቱ ራሱን በሚገባ መግዛትና ታጋሽ መሆን እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ነገር ግን መታገስና ራሱን መግዛት ተስኖት ሲናደድና የሚያስቆጣዉ ነገር ሲገጥመዉ አፉላይ እንደመጣለት ቢሳደብና ከዚያም አልፎ ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት ድብደባ ሆነ ከዛ ያለፈ ወንጀል ቢፈጽም በምድራዊ ሕግ እንደሚጠየቅ ይታወቃል፡፡ ታዲያ በእግዚአብሔርስ ዘንድ

አያስጠይቀዉም ወይ? ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች በፍርድ ቤት ወንጀሉን ስምን እንደፈጸሙ ሲጠየቁ " ተናድጄ ስለነበር፥ ስሜቴን መቆጣጠር ተስኖኝ ነዉ ይህን ያደረኩት፤ አንዳንዶች ደግሞ ሰይጣን አሳስቶኝ ነዉ ይህን የጭከና ድርጊት የፈጸምኩት" የሚሉ አሉና፡፡ እያንዳንዱ ሰዉ ነጻ ሕሊናና ፈቃደኛም ከሆነ እንደ እግዚአብሔር እንዲያስብ፥ እንዲናገር፥ እንዲፈርድ ሙሉ ሥልጣን ተሰቶታል፡፡ ታዲያ ሰዉ ተግድጄ ነዉ ይህን ክህደት የፈጸምኩት፥ ወንጀል የፈጸምኩት፥ ንዴቴን መቆጣጠር ተስኖኝ ነዉ አካለስንኩሉን ቆማጣ ብዬ የተሳደብኩት፥ ዓይነ ስዉሩን እዉር ብዬ የሰደብኩት፥ ዱዳዉን ደንቆሮ ብዬ የሰደብኩት፥ አገሌን የደበደብኩት፥ የገደልኩት … ወዘተ ቢል፤ እዉነተኛ ንስሐ ባይገባና እግዚአብሔርንም ይቅርታ ባይጠይቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ከተጠያቂነትና ከፍርድ ነጻ ነዉ ምንም ንስሐ አያስፈልገዉ ማለት እንችላለን ወይ? በተለያየ የክህደት እምነት ዉስጥ ያሉ ሰዎች ወይንም ቡድኖች "የእኛን እምነት ካልተቀበልክ እንገልሃለን፥ ንብረትህን እንዘርፋለን" ቢሉን ይህን አስገዳጅ ትእዛዛቸዉን ተቀብለን እምነታችንን ብንለዉጥ እንደ ክህደትና ጥፋት ተቆጥሮ አያስጠይቀንም ማለት ነዉን? አለቃችን "ይህን የሐሰት ሰነድ ካለዘጋጀህ ከስራህ ትባረራለህ፥ በሐሰት ትወነጀላለህ" ቢለን እርምጃዉን በመፍራትና እንደ አስገዳጅ ድርጊት ቆጥረነዉ የተባለዉን ትእዛዝ ተግባራዊ ብናደርግ እንደ ኃጢአት አይቆጠረም ወይ?

ሰዎች አንድ ግለሰብን ቤተሰቡ ሆነ ልጆቹ በበሽታና በሌላም ችግር ዉስጥ መሆናቸዉን ተረድተዉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ "አገሌ የተባለ አዋቂ ጋር ብትሄድ ወይንም ብትሄጂ ልጅሽ ይፈወሳል፥ ከችግርህ ከችግርሽ ትላቀቂያለሽ" ቢባል(ብትባል)ና እዉነት መስሏቸዉ አንድ ጠንቋይ ወይንም ቃልቻ(ቃሉ) ጋር ቢሄዱና የተለያየ አምልኮ ባዕድ ቢፈጽሙ እንዲሁም በበላይ ሆኖ ለሚመራቸዉ ዲያብሎስ ቢሰግዱና ቢለማመኑት ከዚያም አልፎ ለችግራቸዉ መፍትሔ እናገኛለን በማለት የተለያየ የደም መስዋዕት ቢያቀርቡ፤ ተታለዉና እዉነት መስሏቸዉ ስላደረጉት እንደ ኃጢአት አይቆጠርባቸዉም፥ ንስሐም አያስፈልጋቸዉም ማለት ነዉን? ስሥጋዉ ያደለ እንደ ሥጋና ደም ሴሜቱ የሚመሳሰለዉ እጅግ ብዙዉ ትዉልድ ለራሱ ጥፋትና በደል ምክንያት እየፈጠረ ከንስሐ የራቀዉ እንደ "ጥፋት፥ በደል፥ ኃጢአት" አይደለም ባልከዉ ምክንያቶች ለበደሉና ለኃጢአቱ ከመጸጸትና ንስሐ ከመግባት ይልቅ ምክንያት እየፈጠረ ከእዉነተኛዉ መንገድ ሲወጣና በበደል ላይ ሌላ በደል በጥፋት ላይ ሌላ ጥፋት ሲፈጽም አይችልም ወይ? ምክንያቱም ሕሊናችን እየመሰከረብንና እየወቀሰን ነዉ ሕሊናችንን በማደንደንና በማታለል የዉሸት እዉነት እየፈጠርን ለጥፋታችን ምክንያት እየሰጠን በዓመፃ ሕይወት የጸናነዉና፡፡ በእኔ አስተሳሰብ ጤነኛ ባላሆነ ባበደ አእምሮ የሚፈጸም ጥፋት ሆነ በደል እንደኃጢአት አይቆጠርም ቢባል እዉነት ይኖረዋል፡፡ ምክንያቱም ያ ሰዉ በነጻ ሕሊናዉ ተመርቶና አገናዝቦ የሚፈጽመዉ መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የለምና፡፡ ከዚያ ዉጭ ያለ ሰዉ ግን ነጻ ሕሊና እግዚአብሔርን የሚመስል አለዉና በዚያ ነጻ ሕሊናዉ አስገዳጅ ነገር ሲገጥመዉ እንኳ እንደ ወልደ ያዕቆብ ዮሴፍ " ይህን ኃጢአት አልፈጽምም"

በማለት መስዋዕትነት መክፈል ይጠበቅበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ እንዲሁም እንደ ሰማዕታት፥ ነቢያት፥ ጻድቃን ፈተናዎችንንና መከራዎችን በትእግስት ማሳለፍና ከዛም በላይ እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንኛዉንም መከራ በአኮቴት መቀበል ይኖርበታል ብዬ አምናለሁ፡፡ ታዲያ የእያንዳንዱ ሰዉ ጽናትና ቆራጥነት ደረጃ መለያየቱን ሳልዘነጋ ነዉ፡፡ ይህ የራሴ እዉቀትና አመለካከት ነዉ፡፡ ሙሉዉን እዉቀትና አመለካከት ግን ካንተ እጠብቃለሁ፡፡

በተረፈ የተለመደዉ ጸሎታችሁ አይለየን ይላል አክባሪህና አፍቃሪህ፥ በቅዱሱ ኪዳን ታናሽ ልጅህና ወንድምህ እንዲሁም የአገልግሎት ባልደረባህ ፈቃደ ሥላሴ፡፡

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር፡፡

ኅዳር ፴፥ ፳፻፯ ዓ. ም.